# Amharic A: literature – Standard level – Paper 1
# Amharique A : littérature – Niveau moyen – Épreuve 1
# Amhárico A: literatura – Nivel medio – Prueba 1

Wednesday 10 May 2017 (afternoon)
Mercredi 10 mai 2017 (après-midi)
Miércoles 10 de mayo de 2017 (tarde)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

### Instructions to candidates

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a guided literary analysis on one passage only. In your answer you must address both of the guiding questions provided.
- The maximum mark for this examination paper is **[20 marks]**.

### Instructions destinées aux candidats

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez une analyse littéraire dirigée d'un seul des passages. Les deux questions d'orientation fournies doivent être traitées dans votre réponse.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d'examen est de **[20 points]**.

### Instrucciones para los alumnos

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un análisis literario guiado sobre un solo pasaje. Debe abordar las dos preguntas de orientación en su respuesta.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es **[20 puntos]**.

2217 – 0011



© International Baccalaureate Organization 2017

https://xtremepape.rs/

ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ ስነጽሁፋዊ ትንታኔ ስጥ። ከታች የተቀመጡትን ጥያቄዎች መመለስ ይኖርብሀል።

**1.**

አንድ ቀን ት/ቤት ውዬ ስገባ ቤታችን ከወትሮው ጭር ብሎ አገኘሁት። በጣም እርቦኝ ስለነበርና፣ ቤት ውስጥ የሚበላ ነገር ፈልጌ ስላጣሁ፣ እዛው ቅርባችን ወደ ምትኖረው የአባቴ እናት ቤት የሚበላ ነገር ለመፈለግ ሄድኩ። እሷም የለችም። የማደርገው ጠፍቶኝ ተበሳጭቼ ቁጭ እንዳልኩኝ ይች አያቴ ከወንዝ ውሃ ቀድታ ስትመለስ አገኘኋት። የሚበላ ነገር እንዳለ ስጠይቃት ከፊቷ በግልጽ ከሚነበብ ንዴት ጋር "ምን እራበኝ ትላለህ ገና አፈር ትበላላችሁ ጉዲና የሞተው ዛሬ ነው" አለችኝ። ግራ በተጋባ መንገድ "ምንድን ነው የሆነው አልኳት" ፍርጥም ብላ የእናቴ አባት ቤት እንዲጠበቁልን ያስቀመጥናቸው በሬዎች በሙሉ እንደተሰረቁ ነገረችኝ። እርሃቡ ወደ ንዴት ሲለወጥ፣ በአእምሮየ ሙሉ የመጣው ቡሬ የአባቴ ትልቁ በሬ ነበር። ቡሬም አለበት? እሱ ካልተሰረቀ የትኛው ሊሰረቅልህ ኖሯል?። ብላ ጥያቄዬን በጥያቄ መለሰችልኝ።

በአባቴ በሬዎች መሰረቅ መጀመሪያ የታየኝ የኢኮኖሚ ጉዳይ አልነበረም። እንደ ታላቅ ወንድሜ የምመለከተው የቡሬ ጉዳይ ነበር። ቡሬ ሰውነቱ በጣም ግዙፍ ስለነበር፣ ዝናብ ሲዘንብ በሱ ስር እጠለላለሁ፣ እራሴንም ሲያሳክከኝ ጭንቅላቴን ወደ አፉ ሳስጠጋው ፍላጎቴ ስለሚገባው በደንብ ይልስልኛል። እኔም ብድሩን ለመመለስ ከእናቴ አሞሌ ጨው እየሰረኩለት ለብቻው አበላው ነበር። ጭድና ለፈረስ ተብሎ የሚታጨድ ሳርም ሰርቄ ለብቻው እሰጠው ነበር፣ በቡሬ መሰረቅ ከልቤ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ። ምንአልባት ከአባቴ መሞት በኋላ በጣም ያለቀስኩት ለቡሬ ነው።

የኢኮኖሚ ጉዳይም ውሎ አድሮ መጣ። በሁለት አመት ገደማ የምንበላለጠው ወንድሜም ሆነ፣ እኔ በደንብ የማረስ አቅም ስላልነበረን በሬዎቻችንን በሬ ለሌላቸው ጥማድ እየሰጠን የምናገኘው ትርፍ እህል ስለጠፋ ድህነት ቤታችን ውስጥ ጠቅልሎ ገባ። በኦሮሞ ባህል ከብቶች ባለቤታቸውን ይከተላሉ ስለሚባል ይሁን፣ አላውቅም አባቴ ትቶልን የሄደው ላሞችም በብዛት አንድ በአንድ በበሽታ እያለቁ ሄዱ። ከዛ በፊት ይቀርቡን የነበሩት ዘመድ አዝማዶቻችንም ሸሹን። በጥቅሉ ኑሮአችን በዛሬው ቋንቋ፣ በፍጥነት የድህነት ወለል ውስጥ ገባ።

በጊዜው ባለስልጣናት ልባቸው ለተማሪ ይራራል ተብሎ ስለሚታመን፣ በአውጫጭኝ በሬዎቼን የማፈላለጉ ሸክም በኔ ላይ ወደቀ። ከ 3ኛ ክፍል እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ለዓመታት ከአጎቴ ጋር ብንንከራተትም በአካባቢው ባላባቶች መመሳጠር የበሬዎቹ ዋጋም በከንቱ እንዲ ጠፋ ተደረገ። ዘላለም ከማያልፍለት የኢትዮጵያ የፍትህ ሥርዓት ጋር በደንብ የተዋወኩት በዛን ጊዜ ነበር። ፋይሌን እንዳይደበቅብኝ ለአውራጃው ገኘ የመዝገብ ቤት ሠራተኛ ሽልንግ (ሃምሳ ሳንቲም) ጉቦ የሰጠሁትም በዛን ጊዜ ነበር። ሃምሳ ሳንቲም የዛሬውን አያድርገውና ቢያንስ ለሁለት ጊዜ የስጋ ምግብ ያበላ ነበር። በገንዘቧ ብቻ ሳይሆን እስከ ዛሬ በሙስና ለተተበተበው የፖለቲካ ስርዓታችንና የፍ/ቤት ስርዓታችንን ለማለፍ የከፈልኳት የመጀመሪያ ጉቦ ስለሆነ አልረሳኋትም።

*መረራ ጉዲና፣ የኢትዮጵያ ፖለቲን ምስቅልቅል ጉዞና የህይወቴ ገጽታች፣* (2006)።

(a) በመራራና በበሬው መንከል ያለው ወዳጅነት ለጽሁፉ ያለው ጥቅም ላይ አስተያየት ስጥ።

(b) ደራሲው ገለፃን በጽሁፉ ለምን አላማ እንደተጠቀመበት አስረዳ።

https://xtremepape.rs/

**2.**

*ፀደያችን ክረምታችሁ መኸራችን መከራችሁ*

ትላንትና ማታ…
ጨረቃና ኮከብ፣ ጨለማን ድል ነስተው
ሲነግሱበት አየሁ…
ደግሞ በማለዳ፣ ወፎቹን ሰምቼ
ተነሳሁ ባትቼ
* * * *
የመስኮቴን ግርዶሽ፣ ገልጬ ሳማትር
የነጋለት ዜጋ፣ ይላል ውትር ውትር
ሲኳትን ሊቀትር
* * * *
የቀተረው ሰማይ
ውሎውን ሲያስረክብ፣ ለምሽት ተረኛ
ጎኑን ያሳርፋል
ነግቶ ጮራ እስከሚያይ፣ የነገ ተስፈኛ
ተስፋማ ዳቦ ነው…
ሲገኝ የሚገመጥ፣ ላይ የተሰቀለ
ታዲያ እንደምን ሆኖ፣ እንዴትስ ቀለለ???
ህልም – ሆኖ – ተስፋ፣ ርቆ እንደሰማይ
ይገኝ በነበረስ፣ ሞልቶ ነበር ከጃይ
እያልኩ ስገረም…
ይህን ሳብሰለስል፣ ከመስኮቱ ቆሜ
ለካ የኔም ተስፋ፣ተሰቅሏል አለሜ
ታድያ ምነው ዝም አልኩ…?
ተስፋዬን በተስፋ፣ ላገኘው አስቤ
በሌሎቹ ተስፋ፣ የኔውን ደርቤ
እኔም በማለዳው፣ ብርሃን ታግዤ
ተስፋን በተስፋዬ፣ ማህፀን አርግዤ
ልሄድ እንጅ ልንጎድ፣ ልጀምር ፍለጋ
በማለዳው ብርሃን፣ በተስፋዬ ምርኩዝ፣
ፊት እየተመራሁ፣ ምሽቱ እንደነጋ
ደግሞ የመሼ እንደሁ…
ሌላ ተስፋ አዝዬ፣ ንጋትን ፍለጋ
ወደፊት… ተስፈኛው ልቤ፣፡፡
* * * *

ዘሃራ ሰኢድ፣ *መናኝ ህልም እና ሳቅ*፣ (2008)፡፡

(a) የግጥሙ ዋነኛ ጉዳይ ወይም መልእክት ምንድነው?

(b) የገጣሚው የቋንቋ አጠቃቀም የግጥሙን መልእክት ለማስተላለፍ እንዴት ጥቅም ላይ ዋለ?

https://xtremepape.rs/